ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 10 ቁጥር 4 የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም.

# መቼ ይሆን?

*ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን 112ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በድጋሚ የተዘጋጀ*

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ* http://www.yatewlid.org/images/mp3/Ya_Tewlid_Vol_10_No_4_March8_112F.mp3

በዓለም ሕዝቦች በተለይ በሴቶች መብት ተቆርቋሪዎችና ደጋፊዎች ዘንድ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1911 ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከበር ለኖረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 (የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም.) 112ኛ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ መልዕክታችን ከ «ያ ትውልድ ተቋም» ይድረሳችሁ።

የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም የሚከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የዓለም ሴቶች በዓሉን ምክንያት በማድረግ አንድነታቸውን፣ ዓላማቸውንና ተስፋቸውን የሚገልጹበት ዕለት ነው። የኢትዮጵያ ሴቶችም በሀገራችን በረሃብ ለሚሰቃዩ፣ ወደ ባዕድ ሀገር በሽያጭ ለሚጓዙ እህቶቻችን፣ ያለ ዕድሜያቸው ለወሲብ ጥቃት ተገደው ለሚደፈሩ ሕፃናት፣ ጧሪ ላጡ አሮጊት እናቶች፣ አሳዳጊ ላጡ ሕፃናት፣ በተለያየ ሕመም ለሚሰቃዩ እህቶቻችን፣ በየእሥር ቤቱ ለሚማቅቁ ሴቶች፣ በስደት ሕይወት ውስጥ ላሉ፣ ማንነትን ተገን ባደረገ የዘር ጭፍጨፋ ክቡር ሕይወታቸውን ላጡና አሁንም ባሰቃቂ አጣብቅኝ ውስጥ ያሉትን ወገኖች፤ በአጠቃላይ ግፈኛና ዘረኛ አገዛዝ በሴቶች ላይ ያሳረፈውን መከራና ጫና ለመታገል አንድነታችንን የምናጠናክርበት ወቅት ላይ መድረሳችንን ትኩረት በመስጠት ነው።

ማርች 8 ለሴቶች ሀገራቸውን እና ሕዝባቸውን የሚያዩበት ቀን ናት። ማርች 8 ሴቶች ለሰው ልጆች የዜግነት መብትና ነፃነት የሚሞግቱበት ቀን ናት። ማርች 8 ሴቶች ከጀግና እናት አባቶቻችን የወረስነውን አኩሪ የሀገር ፍቅር ቅርስ ለትውልድ የምናስተላልፍበት ቀን ናት። ማርች 8 ለእናት ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቧ እኩልነት ድምጻቸውን ባሰሙ ደማቸው ለፈሰሰው፣ አጥንታቸው ለተከሰከሰው ወገኖቻችን በተለይ ሰማእት ሴቶችን የምንዘክርበት ቀን ነው።

ከኅብረተሰባችን መሃል የኢትዮጵያ ሴቶችን ነጥለን ስንቃኝ ስለ እኛ ሴቶች ገና አልተጻፈም፣ አልተነገረም፣ አልተተረከም ብንል ስህተት አይሆንም። ሴቶች ስንል በይበልጥ እናትነት ስለሚመጣብን እናቶቻችን ትዝ ይሉናል። እኛን ለማሳደግ የከፈሉት መከራና፣ ጥረት ይታወሰናል። ዕድሜ እየጨመርን ብንሄድም ለነሱ ሁሌ ልጅ ነን። የወጣት ሴቶች እህትነት፣ ጓደኝነት፣ ፍቅረኝነት ሁሌም አብሮን አለ። በጥቅሉ ሴት የኅብረተሰቡ ዋልታና ምሰሶ ናት ብንል ማጋነን አይሆንም።

ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ማርች 8 ስንዘክር የሴት ልጅ በደል፣ ጭቆና፣ ስቃይ፣ መከራ፣ አድልዎ፣ ልቅሶ መሰል ቃላቶች ይወሩናል፤ ይመጡብናል። “ያ ትውልድ ተቋም” ማርች 8ን እና ሴቶችን ስናስታውስ የወጣት ሴቶች ከፆታ መብት ጥያቄ ባለፈ መልኩ ለሀገርና ለሕዝባቸው ያደረጉት የዴሞክራሲያና የፍትህ ትግል አስተዋጽዖና የከፈሉት መስዋዕትነት ሁሌም አብሮን አለ።

*ለሀገራቸው አንድነትና ነጻነት በጠላት ወረራ ጊዜ በጠላት ውስጥ የውስጥ አርበኛ በመሆን መረጃ በመሰብሰብ ትልቁን ድርሻ የተወጡ በርካታ ናቸው። በአድዋ ጦርነት በየአቅጣጫው ወደ ወረሂሉ ከተመመው ሠራዊት ጋር ጋራና ሸንተረሩን፣ ሸለቆና ቁጥቋጦውን፣ ወንዝና ጅረቱን፣ ተቋቁመው ምግብ እያዘጋጁ፣ እያበሰሉ፣ እየመገቡ፣ እንደገና ለቀጣዩ ቀን እየተሸከሙ አምስት ወር ቀንና ለሊት ሲጓዙ፣ ወደ 3 ወር የመልስ ጉዞ የከፈሉት መስዋዕትነት ለጦርነቱና ለተገኘው ድል ያበረከተው ድርሻ እንዴት ጠንካራ እንደነበር መገመት አዳጋች አይደለም።*

*ከአባት እናቶቻችን የወረስነው የሀገር፣ የሰንደቅ ዓላማና፣ የሕዝብ ፍቅር በያ ትውልድ ሴቶች እጅጉን ተመስክሯል። በ1960 ዎቹ ያ ትውልድን ያደመቁት፣ ከትግሉ ጫፍ ብቅ ያደረጉት "ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ" እንደተባለው "ያለሴቲቱ አይሠምር ሂደቱ" እንበልላቸውና ትግሉን ማድመቅ ብቻ ሳይሆን መርተዋል፣ ታግለው አታግለዋል፣ "የትግሉ ነው ሕይወቴ" ብለው ተሰውተዋል።*

*ማርች 8 በአገራችን ኢትዮጵያ መከበር ከጀመረበት 1968 ዓ.ም. ጀምሮ እየተቀጣጠለ በመጣው የዴሞክራሲ መብትና የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ወጣት ሴቶች በድርጅታቸው ኢሕአፓ አማካይነት በፓርቲው፣ በወጣት ሊጉ፣ በኢትዮጵያ ሴቶች ትግላዊ ድርጅት (ኢሴትድ) በከተማው እንዲሁም በገጠሩ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) በመሳተፍ በትግሉ ያላቸውን ብቃት አስመስክረዋል። መስዋዕትነት ከፍለዋል።*

*ደርግ ሕዝባዊ ትግሉን ለማኮላሸት በነደፈው "መንጥር ዘመቻ" በቤት ለቤት አሠሳ፣ ነፃ እርምጃ፣ ቀይ ሽብር ተደጋጋሚ እሥር፣ ስቃይና ጭፍጨፋ ሴቶች ለማመን በሚያዳግት መልኩ ተሰቃይተዋል፣ ተሰደዋል፣ መስዋዕትነት ከፍለዋል። በዚህ ዘመን እናቶች ከማንም ባላነሰ የስቃዩ ተካፋይ ነበሩ። በትግሉ ወቅት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረጉ እናቶች በቀይ ሽብር ወቅት ደግሞ መሪር ሀዘን፣ ጭንቀት፣ ስቃይ፣ መመሰቃቀል አግኝቷቸዋል። ይሄዳሉ እንጂ ወዴት እንደሚጓዙ አያውቁትም፣ ምግብ ያቆሙ፣ መንገድ ሲሄዱ መለፍለፍ፣ መኝታቸውን መሬት ያደረጉ፣ እንቅልፋቸው ቅዠት የነበር በርካቶች ነበሩ። በቤት ለቤት አሰሳና በነፃ እርምጃ የት እንደደረሱ ያላወቋቸው ልጆቻቸው ስቃይ ላይ በቀይ ሽብር የታሰሩባቸው ልጆቻቸው ህልምና ቅዠት ሕይወት ውስጥ ከቷቸዋል። ቀን ለቀን በጠራራ ፀሐይ እየተዘዋወሩ "የኔ ልጅ ይሆን/ትሆን?" ብሎ መንገድ ላይ የተጣለ ሬሳ ማገላበጥ ከእብደት ያላነሰ ዓለም ውስጥ ከቷቸዋል። ለሊቱ መሽቶ እስኪነጋ "ልጄ እንዴት አድሮ/አድራ ይሆን?" ሀሳቡ እንቅልፋቸውን ወስዶ በደመነፍስ ከእስር ቤቱ ደጃፍ ደርሰው የልጃቸው ሳህንና ልብስ ይመለስላቸዋል። ሰቆቃው እና ምሬቱ ተነግሮና ተጽፎ አያባራም። ይህ ሰቆቃ ዛሬ በተለይ የኢትዮጵያ ሴቶች ማርች 8ን ስናከብር ሊዘነጋን አይገባም።*

*የታሪክ ድግምግሞሽ ያልተለያት ሀገራችን በኢሕአዴግ/ህወሓት አገዛዝ በርካታ ሴቶች ለሀገራቸው ሲሉ ታስረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ተሰደዋል። የዚህ ሰቀቀን ዳግም እናቶችን እየዬ አሰኝቷል። ዛሬ ዛሬ ደግሞ ግድያና ግፍ አድማሱን አስፍቶ እናት ከነልጆቿ ምትገደልበት፣ በእሳት ምትጋይበት፣ ምትታረድበት የጉድ ዘመን አድርሶናል። በየጊዜው እድገት የሚያሳየው የኑሮ ውድነትና ድህነት ሴቶችን ለስደት መዳረግ ብቻ ሳይሆን ለሞትና ለአካል ጉዳት መዳረጉ የትላንት ሳይሆን የዛሬም ክስተት ነው። ኑሮን ለመቋቋም፣ ቤተሰብን ለማቃመስ ሲሉ ሳይወዱ በግድ ገላቸውን ሚቸረችሩ ሴቶች ስቃይ መች ይሆን የሚበቃው? ያሰኝናል። መማር እየፈለጉ፣ እንደ ልጅነታቸው መጫወት እያማራቸው ወላጆቻቸውን ዳቦና ቆሎ ለማቃመስ በየጎዳናው "ጋሼ፣ እሙዬ" እያሉ እጃቸውን የሚዘረጉ ታዳጊ ሕጻናት መቼ ይሆን ደብተርና እርሳስ የሚይዙት? እህቶቻችን እንደሸቀጥ ገንዘብ ያለው ቱጃር ሚጫወትባቸው መጨረሻው መቼ ይሆን? ሊታሰብ የማይችል፣ በባህላችን ከቶም የሌለ ሕጻናት ሴቶችን ጨምሮ ሴቶችን አስገድዶ መድፈር የት ጋ ነው ማብቂያው?*

*"ያ ትውልድ ተቋም" የዘንድሮውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ስናከብር የሴቶችን ተጋድሎ ብንዘክርም ሀገራችን ላይ በይፋ የሚታየውን በማንነት ላይ ያተኮረ ጭፍጨፋንና ዘረኝነት የፈጠረው ሴቶቻችን ላይ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ግፍ ማስተጋቢያ አድርገነዋል። የእናቶች ልቅሶ፣ የሴቶች ግፍ፣ የሕፃናት ስቃይ መድረኩን በሞላባት ሀገር*

“የሴቶች ቀን” ብለን ቀኑ ጨለማ የሆነባቸውን ሴቶቻችንን ማየት ፈለግን። የሴቶች ቀን ብለን “ባለቤቴንና ልጆቼን እያየሁ ፊቴ ገደሏቸው” የምትለውን እናት ሰቆቃ ማድመጥ አሰብን። “ወንድምና አባቴን ገድለው እኔን አሰቃይተው ጥለውኝ ሄዱ” ምትለዋን ተስፋዋን ያጣች ወጣት መጣችብን። እየተንሰቀሰቀች በኮልታፋና ጣፋጭ አንደበቷ “አባትም እናትም የለኝም፣ ሁሉንም ገደሏቸው” እያለች እምባዋን ምታፈስዋ ታዳጊ አሳዘነችን። “እኔ ወደ ጫካ ተደብቄ ተረፍሁ ሚስቴንና ሴት ልጆቼን ከነቤቱ አቃጠሏቸው” ለሚለው አባወራ ለሱም ለቤተሰቡም እግዚኦ! አልን።

አንተ የሕጻናት አምላክ! ስለ ወላዲቷ ማርያም ብለህ በእናቶች፣ በሴቶች እና በሕጻናት ላይ ለሚደርሰው መከራ “በቃ በለን!” አልን። እመ ብርሃን ሆይ! ለእኛ ሲል ስለተሰቃየውና ስለተሰቀለው አንድ ልጅሽ ብለሽ “ምልጃሽ አይለየን” አልን!

“ያ ትውልድ ተቋም” ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናከብር በትንሹ ለግማሽ ምእተ ዓመት የቀጠለውና አድማሱን እያሰፋ የመጣው የሴቶች የእንግልት ሕይወት ከአጠቃላይ የሀገራችን ሕዝብ ስቃይ ተነጥሎ የማይታይ የብልሹ አገዛዞች ውጤት ቢሆንም ቀኑ ስለሴቶች፣ በሴቶች ድምጽ የምናሰማበት እለት ነው።

ስለ ሕጻናት ልቅሷችን ያብቃ! የምንልበት ነው። እምባችንን የሚያብስ የፍትህና የዴሞክራሲ ዘመን ያምጣልን! እያልን ነው። ለልጆቿ በልጆቿ ለሆነች ኢትዮጵያ እምባችን መሠረት ይሁናት! እያልን ነው።

በሴቶች ተሳትፎ የኢትዮጵያችን አንድነት ያብባል!!

ማርች 8 ሰማዕታት እህቶቻችን ሚታወሱበት!

***«ያ ትውልድ ተቋም»***

**የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም.** (March 8, 2023)

ኢሜል : yatewlid@gmail.com
ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
ምስለ ገጽ : https://www.facebook.com/yatewlid.thegeneration